የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ – ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 42
ADDIS ABABA–11th June, 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፲፮/፲፱፻፺ ዓ·ም·
የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ) አዋጅ ................ ገጽ ፯፻፶፪

## CONTENTS

Proclamation No. 116/1998
Investment (Amendment)
Proclamation ........................................ Page 752

### አዋጅ ቁጥር ፻፲፮/፲፱፻፺

### የኢንቨስትመንት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢንቨስትመንት አዋጅ እንዲሻሻል ማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፻፲፮/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፹፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩· የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተተክቷል፤

"፭· 'የአገር ውስጥ ባለሀብት' ማለት የኢንቨስትመንት ካፒታል በሥራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም መደበኛ ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን መንግሥትንና የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንዲሁም እንደአገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋን ይጨምራል፤"

### PROCLAMATION NO.116/1998
### A PROCLAMATION TO AMEND THE INVESTMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Investment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Investment (Amendment) Proclamation No.116/1998."

2. *Amendment*

The Investment Proclamation No.37/1996 is hereby amended as follows:

1) Sub-Article(5) of Article 2 of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article(5):

"5. 'Domestic Investor' means an Ethiopian or a foreign national permanently residing in Ethiopia having made an investment and includes the Government, public enterprises as well as a foreign national, Ethiopian by birth, and desiring to be considered as a domestic investor,"

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· የአዋጁ አንቀጽ ፭ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፭ ተተክቷል፤

"፭· ለመንግሥት የተከለሉ የሥራ መስኮች

፩· የሚከተሉት የሥራ መስኮች በመንግሥት ብቻ የሚካሄዱ ይሆናሉ፤

ሀ) የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትን ሳይጨምር፤ ከ፳፭ ሜጋዋት በላይ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨትና የማከፋፈል ሥራ፤ እንዲሁም በተያያዙ ዋና ዋና መስመሮች የኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፍና የማከፋፈል ሥራ፤

ለ) ከ፳ መንገደኞች ወይም ከ፪ሺ፯፻ ኪሎ ግራም በላይ የመጫን አቅም ባላቸው ኤርክራፍት የሚካሄድ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፤

ሐ) የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት፤

መ) ፈጣን የፖስታ አገልግሎትን ሳይጨምር የፖስታ አገልግሎት።

፪· በሚከተሉት የሥራ መስኮች ባለሀብቶች ኢንቨስት ለማድረግ የሚችሉት ከመንግሥት ጋር በመቀናጀት ብቻ ይሆናል፤

ሀ) የመከላከያ ኢንዱስትሪ፤

ለ) የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት።"

፫· የአዋጁ አንቀጽ ፮ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፮ ተተክቷል፤

"፮· ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች

፩· የሚከተሉት የኢንቨስትመንት መስኮች ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባላቸው ባለሀብቶች ብቻ የሚካሄዱ ይሆናሉ፤

ሀ) የባንክና የኢንሹራንስ ሥራ፤

ለ) የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትን ሳይጨምር ፤ እስከ ፳፭ ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨትና የማከፋፈል ሥራ፤

ሐ) እስከ ፳ መንገደኞች ወይም እስከ ፪ሺ፯፻ ኪሎ ግራም የመጫን አቅም ባላቸው ኤርክራፍት የሚካሄድ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፤

መ) የፎርዋርዲንግና ሺፒንግ ኤጀንሲ አገልግሎቶች፤ ሆኖም መንግሥት በተለየ ሁኔታ ሲፈቅድ ለውጭ ባለሃብቶችም ክፍት ይሆናሉ።

፪· በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት መስኮች ዝርዝር በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

፫· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በሌሎች መስኮች ኢንቨስት ከማድረግ አይከለክላቸውም።"

፬· የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል፤

"፬· በኢንጂነሪንግ ፣ በአርኪቴክቸራል ወይም በሌላ የቴክኒክ ምክር አገልግሎት፤ በሂሣብና በኦዲት አገልግሎት ፤ በፕሮጀክት ጥናት ወይም በንግድ ሥራና ማኔጅመንት የምክር አገልግሎት መስክ ኢንቨስት የሚያደርግ የውጭ ባለሀብት የሚጠየቀው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን ፩፻ ሺህ የአሜሪካን ዶላር ይሆናል።

፭· በአዋጁ አንቀጽ ፳፰ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲) ተጨምሯል፤

2) Article 5 of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Article 5:

"5. Areas of Investment Reserved for the Government

1) The following investment areas are exclusively reserved for the Government:

(a) excluding generation of electricity from hydropower; generation and supply of electricity above an installed capacity of 25 megawatts as well as transmission and supply of electrical energy through the Integrated National Grid System;

(b) air transport services using aircraft with a seating capacity of more than 20 passengers or with a cargo capacity of more than 2,700 kg.;

(c) rail transport services;

(d) postal services with the exception of courier services.

2) Investors shall be allowed to invest in the following areas only in partnership with the Government:

(a) defence industries;

(b) telecommunication services."

3) Article 6 of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Article 6:

"6. Areas of Investment Reserved for Domestic Investors

1) The following investment areas are exclusively reserved for Ethiopian Nationals:

(a) banking and insurance business;

(b) excluding generation of electricity from hydropower; generation and supply of electrical energy up to 25 megawatts;

(c) air transport services using aircraft with a seating capacity of up to 20 passengers or with a cargo capacity of up to 2,700 kg.;

(d) forwarding and shipping agency services; provided, however, where the Government permits otherwise, same shall be open for foreign investors as well.

2) The investment areas exclusively reserved for domestic investors shall be determined by Regulations issued by the Council of Ministers.

3) Nothing in this Article shall be construed to exclude domestic investors from investing in other areas of investment."

4) Sub-Article(4) of Article 11 of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article(4):

"4) The minimum capital required of a foreign investor investing in areas of engineering, architectural or other technical consultancy services; in accounting and audit services; in project studies or business and management consultancy services shall be 100,000 US Dollars."

5) The following new sub-Article(10) is added under Article 28 of the Proclamation:

"፲· አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ መሠረት ከሚፈቀደው የተለየ ወይም ተጨማሪ የሆነ ማበረታቻ እንዲሰጥ በመወሰን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል።"

፮· በአዋጁ አንቀጽ ፴፯ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፤

"፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የውጭ ባለሀብት በራሱ ባለቤትነት ወይም አብዛኛውን የባለቤትነት ድርሻ በመያዝ ለሚያካሂደው ድርጅት የባለ ሥልጣኑን ስምምነት በቅድሚያ በማግኘት የውጭ ዜግነት ያላቸው ከፍተኛ የማኔጅ መንት አባላትን ለመቅጠር ገደብ አይደረግ በትም።"

፯· ከአዋጁ አንቀጽ ፴፰ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፱ ተጨምሯል፤

"፴፱· <u>የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለቤትነት ስለመያዝ</u>

በፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር ፫፻፺ – ፫፻፺፫ የተደነገገው ቢኖርም፣ የውጭ ዜጋ የሆነ ባለሀብት ለኢንቨስትመንት ሥራው የሚያ ስፈልገውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለቤ ትነት ሊይዝ ይችላል።"

፰· የአዋጁ አንቀጽ ፴፱፣ ፵፣ ፵፩ እና ፵፪ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፵፣ ፵፩፣ ፵፪ እና ፵፫ ሆነዋል።

፱· ከአዋጁ ጋር የተያያዘው ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮችን የሚዘረዝረው ሠንጠረዥ ተሠርዟል።

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

"10) Whenever it deems it necessary, it shall decide on new or additional incentives, other than what is provided under the Investment Incentives Regulations and submit same to the Council of Ministers for approval."

6) The following new sub-Article(3) is added under Article 37 of the Proclamation:

"Notwithstanding the provisions of sub-Articles(1) and (2) of this Article, a foreign investor upon obtaining the prior consent of the Authority shall, without any restriction, have the right to recruit expatriate employees on top management positions of an enterprise of which he is the sole or major owner."

7) The following new Article 39 is added after Article 38 of the Proclamation:

"39. Ownership of Immovable Property

Notwithstanding the provisions of Articles 390-393 of the Civil Code, investors of foreign nationality can own immovable property requisite for their investment activities."

8) Articles 39, 40, 41 and 42 of the Proclamation are re-numbered as Article 40,41,42 and 43, respectively.

9) The Schedule on investment areas reserved for domestic investors, attached to the Proclamation, is hereby deleted.

3. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 11th day of June, 1998.

Done at Addis Ababa, this 11th day of June, 1998.

NEGASO GIDADA(DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA